
# ክፍል 3
## ህንፃ እና ግንባታ

PK4



AppleTree

EVERY CHILD READY @Home

# ክፍል 3

## ህንፃ እና ግንባታ

AppleTree

©2020
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። ከዚህ በታች በቅጂ መብት የተያዙትን መብቶች ሳይገድብ ፣ የትኛውም የዚህ ህትመት ክፍል እንደገና ሊባዛ ፣ ሊከማች ወይም ወደ ሌላ የማስመለሻ ስርዓት ሊተላለፍ አይችልም ፣ ወይም በማንኛውም መልኩ ወይም በማንኛውም መንገድ (ኤሌክትሮኒክ ፣ ሜካኒካል ፣ ፎቶ ኮፒ ማድረግ ፣ መቅዳት ወይም በሌላ መንገድ) ያለ ቅድመ የጽሁፍ ፈቃድ ።

AppleTree Institute for Education Innovation
1801 Mississippi Ave SE, 3rd Floor
Washington, DC 20020

የቅጂ መብት © 2020 ጽሑፍ እና ስዕሎች። AppleTree Institute(አፕል ትሪ ኢንስቲትዩት) መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

# PK4 ክፍል 3 አጠቃላይ እይታ



## ክፍል 3
## የቃላት ዝርዝር

- የመዝናኛ መናፈሻ
- ንድፍ
- ድልድይ
- ህንፃ
- ግንባታ
- ስሜቶች
- ግብ
- ችግር
- መወጣጫ
- መንገድ
- መሣሪያ

**ውድ ቤተሰቦች,**

ወደ ክፍል 3 እንኳን በደህና መጡ! በክፍል 3 ውስጥ ልጅዎ ስለግንባታ ሂደት - ንድፍ ማዘጋጀትን ፣ የግንባታ ሰራተኞችን እና የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎችን በማካተት ይማራል።

## ክፍል 3 መፅሃፍ



- *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ* በ (Felicia Truong) ፌሊሺያ ትሩንግ
- *(Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ* በ (Felicia Truong) ፌሊሺያ ትሩንግ
- *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር* በ (Julie Fowler) በጁሊ ፎውለር
- *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት* በ (Mitchell Stevens) ሚቼል ስቲቨንስ

*ECR @ የቤት ውስጥ ተግባራት ድልድዮችን መንደፍ እና መገንባት ፣ ቅርጾችን መደርደር ፣ እስከ 15 ድረስ መቁጠር እና ስለ ጣራዎች ፣ መሰረቶች እና መንገዶች ለማወቅ ሙከራዎችን ማካሄድን ያጠቃልላል ። እንዲሁም ስለ ሰዎች ስሜት ማሰብ ይጀምራሉ ፣ የመገለል ስሜትን ፣ እንዲሁም በስኬታቸው የኩራት ስሜት እንዲሰማቸው ይሆናል ።*


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሳምንት 1


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# PK4 ክፍል 3 ሳምንት 1 አጠቃላይ እይታ

## መዋቅሮች እና ሕንፃዎች



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ ይህንን ይማራል፡

ስለ አንድ ሕንፃ መሠረት ማወቅ እና ስለ ታሪክ ችግሮች እና ግቦች። እንዲሁም እስከ 15 ድረስ በመቁጠር እና ቅርጾችን መደርደር ይማራሉ ።.

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



## ህንፃ

ጣራ እና ግድግዳ ያለው ቤት የመሰለ ቦታ




## ግብ

ለማግኘት የሚፈልጉት ነገር እና ለማግኘት ወይንም ለማድረግ የሚሞክሩት



## ችግር

የሆነ ትክክል ያልሆነ ነገር ሲኖር


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

## አስብበት!

በዚህ ሳምንት ስለ ሕንፃዎች ይማራሉ። ፓኬቱን ከመጀመርዎ በፊት ምን ዓይነት ሕንፃዎች እንደሚወዱ ያስቡ። የእርስዎን ተወዳጅ ሕንፃ ይሳሉ።



©2020. All Rights Reserved. AppleTree Institute. Every Child Ready.

# ሰኞ



## STEM: ቅርፆችን መደርደር


**ቁሳቁሶች**: **ቅርፆች** ወደ ካርዶች መቁረጥ



- ከልጅዎ ጋር በካርዶቹ ላይ የተለያዩ ቅርጾችን ይሰይሙ ።
- ይህን ይበሉ, **ተመሳሳይ የሆኑ 2 ቅርጾችን ፈልገህ በአንድ ላይ አጣምራቸው ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ሌሎች ቅርጾችን እንዲለይ ያድርጉት ።
- በዚህ ክፍል ውስጥ ለሚገኙ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ቅርፆቹን ያስቀምጧቸው።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ የህንፃ ቅርፅ

**ቁሳቁሶች**: **የህንፃ ቅርፆች, ግሉ, መቀሶች, ወረቀት**



- ለልጅዎ ቅርጾችን ይቁረጡ ። ይህን ይበሉ, **ሕንፃ ለመሥራት እነዚህን ቅርጾች ማጣበቅ ትችላለህ ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ በራሱ ፈጠራ ሕንፃውን እንዲሠራ ያድርጉ።
- ከዚያ በኋላ ስለተጠቀሙባቸው ቅርጾች ይነጋገሩ ። ይህን ይበሉ ፣ **ነገ እንደ በሮች እና መስኮቶች ያሉ መገልገያዎችና ትጨምርበታለህ።**
- ሕንፃውን ለነገው የመገልገያዎች የግንባታ እንቅስቃሴ ይሆን ዘንድ ያስቀምጡት ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሰኞ


PK4 ክፍል 3 ሳምንት 1 ቀን1

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: ምንድነው ችግሩ?

- ይህን ይበሉ ፣ **ችግር ማለት የሆነ ነገር ትክክል ያልሆነ ነገር ሲኖር ነዉ ። ችግር አጋጥሞህ ያውቃል?**
- ከልጅዎ ጋር ስለችግራቸው እና ችግሩን ለመፍታት ሲሞከ ክሩ ስላደረጉት ድርጊት ያነጋገሩ ። እንዲሁም ምሳሌ ለመስጠት ያህል ስለነበረብዎት ችግር ማጋራት ይችላሉ።


## አንብብ: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears)* ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ

**ቁሳቁሶች**: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*, **አማራጭ - *የመለኪያ ቴፕ ወይንም* *ማስመሪያ***





- ከልጆ ጋር, ያንብቡ *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*
- ከዚያ በኋላ ስለ መለኪያ ቴፕ አንድ ላይ ይነጋገሩ። ይህን ይበሉ ፣ **አንድ ነገር ምን ያህል ፣ ሰፊ ወይም ረዥም እንደሆነ ለመለካት የመለኪያ ቴፕን እንጠቀማለን። ግንበኞች እንደ እንጨት ያሉ ነገሮችን ከመቁረጣቸው በፊት ለመለካት ይጠቀሙበታል ። እንዲሁም የክፍሉን መጠን መለካት ይችላሉ ። ሉ ሉ የመለኪያ ቴፑን ምን ለመለካት ነው የተጠቀመው?**
- የመለኪያ ቴፕ ወይም ማስመሪያ በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን እንዴት እንደሚለኩ ለልጅዎ ማሳየት ይችላሉ ።



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.





© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ማክሰኞ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 1  ቀን2

## **STEM:** የህንፃ መሰረት

**ቁሳቁሶች: የመጫወቻ ሊጥ, የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት ,**
**የቤት እቃዎች እንደ ዱላዎችን ፣ የጥጥ ንጣፎችን ፣ ማንኪያዎችን ፣ ወዘተ**


የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።

- ይህን ይበሉ, **የህንፃ መሠረት፣ ህንፃው ጠንካራ እንዲሆን እና እንዲቆም  የሚረዳው የታችኛው ክፍል ነው፡፡** ከልጅዎ ጋር በስልክ ወይም በታብሌት ላይ የህንፃ መሠረት ምስሎችን ይመልከቱ ፡፡
- ይህን ይበሉ, **የሕንፃ ግድግዳዎች መሠረት ከሌላቸው ምን እንደሚሆን እስቲ እንመልከት ፡፡**
- ከልጅዎ ጋር ፣ዱላዎቹ እራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ ለማድረግ ይሞክሩ፡፡ ለምን ሊቆሙ እንዳልቻሉ ይናገሩ ፡፡
- ከዚያ፣ ይህን ይበሉ፣ **እስቲ ይህን የመጫወቻ ሊጥ እንደ ሲሚንቶ የሕንፃው መሰረት ነው ብለን እናስብ፣ እና የዱላ ግድግዳችንን በውስጡ ለማስገባት እንሞክር፡፡** ከዚያ በኋላ፣ ከመጫወቻ ሊጡ  እና ያለሱ በግድግዳዎች ላይ ስለደረሰው ነገር ይናገሩ ፡፡

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ የህንፃ መገልገያዎች

**ቁሳቁሶች: በመጀመሪያው ቀን ላይ የተሰራው የህንፃ ቅርፅ, ማርከሮች ወይም ከለሮች, ግሉ, መቀሶች, ቀለም, አማራጭ -** ***የመፅሄት ስዕሎች የሕንፃ መገልገያዎችን እንደ በር ያሉ ነገሮች ያሉበት***

- ይህን ይበሉ, **እንደ በሮች እና መስኮቶች ባሉ የተለያዩ ክፍሎች ህንፃዎን ቀለም መቀባት እና መጨረስ ትችላለህ ፡፡**
- መገልገያዎቹን በመሳል ወይም በማጣበቅ ልጅዎ ራሱን ችሎ እንቅስቃሴውን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ፡፡
- ከዚያ በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ህንፃዎ እና ስለጨመርካቸው ክፍሎች ንገረኝ ፡፡**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.


# ማክሰኞ



## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የታሪክ ችግር

**ቁሳቁሶች**: ችግር

- ይጠይቁ, **ችግር ምንድነው? ችግር ማለት አንድ ነገር ትክክል ባልሆነ ጊዜ ማለት ነው።**
- ስዕሉን ያሳዩ እና ይህን ይበሉ, **(Emma) ኤማ መወዛወዝ ትፈልጋለች ፣ ነገር ግን ዥዋዥዌው ለእሷ በጣም ወደ ላይ ከፍ ያለ ነው።**
- ይጠይቁ, **ችግሩ ምንድነው? አዎ ፣ ዥዋዥዌው ለእሷ በጣም ወደ ላይ ከፍ ያለ ነው ። ዥዋዥዌው ላይ መውጣት አትችልም ።**




ችግር (FE)

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የኔ ከተማ

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የእኔ ከተማ ጆርናል ገጽ**

- ከልጅዎ ጋር ስለ ከተሞች እና በከተሞች ውስጥ ስለሚገኙ የሕንፃዎች ዓይነት ይነጋገሩ ። የከተሞችን ሥዕሎች በስልክ ወይም በታብሌት ላይ ማየት ይችላሉ ።
- ልጆ የራሱን ከተማ መገንባት ቢችል ፣የእሱ ከተማ ምን ሊመስል እንደሚችል ራሱን ችሎ እንዲሳል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ከተማህ ንገሩኝ ። በውስጡ ምን ዓይነት ሕንፃዎች አሉ?**





© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ። ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ።
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ። አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።






© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ስም: _________________


ከተማ መገንባት ቢችሉ ኖሮ ምን ሊመስል ይችል ነበር?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ




## STEM: ቁጥር የማዛመድ ጨዋታ




**ቁሳቁሶች**: **2 ስብስቦች** 0-5 ቁጥር ካርዶች

- አንዱን የቁጥር ካርዶች ሰብሰብ እንዲታይ አድርገው በጠረጴዛው ላይ ያስቀምጡት ፣ ሌላኛውን የቁጥር ካርዶች ስብስብ በመያዣ ውስጥ ያኑርዎት ። የቁጥር ካርድ ይያዙ። ይጠይቁ ፣ **ይህ ቁጥር ስንት ነው? ሌላ ቁጥር ___ ማግኘት ትችላለህ?** ልጅዎ ቁጥሩን እንዲያገኝ እና ከዚያ ቁጥሩን በጣቱ ትሬስ እንዲያደርግ/ እንዲከታተል ያበረታቱት።
- ሌሎቹን የቁጥር ጥንዶች በማዛመድ ፣ ቁጥሮቹን በመሰየም እና በጣቶቻቸው በመከታተል ልጅዎ ራሱን ችሎ እንቅስቃሴውን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉት ።
- ሁሉንም ቁጥሮች ካላወቁ እና የእርዳታዎን ከፈለጉ ፣ ችግር የለውም።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ የግንባታ ተሽከርካሪዎችን ቀለም መቀባት




**ቁሳቁሶች**: የግንባታ ተሽከርካሪዎችን ቀለም መቀባት, **ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር ስለ ግንባታ ተሽከርካሪዎች እና ስለሚሰሩት ነገር ይነጋገሩ ።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ የግንባታ ተሽከርካሪዎችን ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- ከዚያ በኋላ, ይጠይቁ, **የትኛውን ተሽከርካሪ ማሽከርከር ትፈልጋለህ? ለምን?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 1  ቀን3

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የታሪክ ችግር ክለሳ


**ቁሳቁሶች**: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*



- ይህን ይበሉ, **ሙሉ መጽሐፉን በኋላ ላይ እናነባለን ። በመጀመሪያ ፣ ይህንን ገጽ እንመልከት። ችግሩ ምንድን ነው?**
- የ*(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ* ገፅ. 26-27  ያንብቡ።
- ይጠይቁ, **ችግሩ ምን ነበር?  አዎን ፣ አንድ ሰው በድቦች ወንበር ላይ ነበር እና የህፃኑን ድብ ወንበርን ጭቃ አድርጎበታል።**

## Read: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears)* ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ

**ቁሳቁሶች**: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*




- ከልጆ ጋር, ያንብቡ *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*
- ከዚያ በኋላ, ይጠይቁ, **በታሪኩ ውስጥ ችግሩ ምን ነበር?**
- **(Lou Lou) ሉ ሉ ቤታቸውን ስላቆሸሸባቸው ድቦቹ አንድ ችግር ገጥሟቸዋል ።  የሕፃን ድብን ገንፎ በልታ ወንበሩን እና አልጋውን ጭቃ አደረገችው ።.**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 1  ቀን3

## እንቀሳቀስ፡ የግንባታ በምልክት የማስመሰል ጨዋታ

- ይህን ይበሉ, **ጨዋታ እንጫወት።  አንዳችን የአንድን የግንባታ እርምጃን የምንከውን ሲሆን ሌላኛው ሰው ምን እንደ ሆነ ይገምታል ።**
- ተራ በተራ በመቀያየር የተለያዩ ድርጊቶችን እንደ ሚስማር በመዶሻ መምታት፣ እንጨት መሰንጠቅ ፣ እንደ ባክ ሆ/ትራክተር መቆፈር ፣ ነገሮችን እንደ ክሬን ማንሳት ፣ ወዘተ..

## በጋራ መማር፡ ኩራት ይሰማኛል

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር ፣ በኩራት ስሜት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ይነጋገሩ።  ይህን ይበሉ ፣ **ኩራት ማለት በሠራኸው ነገር ደስተኛ መሆን ማለት ነው ።  እንዲሁም በሌሎች ሰዎች ኩራት ሊሰማህ ይችላል።  እኔ በአንተ እኮራለሁ ምክንያቱም _________.**
- ይህን ይበሉ, **ስለ ሞትኮራበት አንድ ነገር ስዕል ሳል ።**
- ልጅዎ ስዕሉን ከሳሉ በኋላ ስለ ስዕሉ እና ስለ ኮሩበት ነገር ይንገርዋ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

1

2

3

4

5


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

1

2


3

4

5



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ባክ ሆ





© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ቆሻሻ መጣያ መኪና




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሲሚንቶ ማቡኪያ መኪና




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሐሙስ


PK4 ክፍል 3 ሳምንት 1  ቀን4

## **STEM:** የህንፃ ጥንካሬ

**ቁሳቁሶች**: paper, **እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ነገሮች እንደ የወረቀት ፎጣ ጥቅልሎች ፣ ትናንሽ የፕላስቲክ መያዣዎች**

- ይህን ይበሉ, **አንድ ነገር አንድ ላይ ሆነን እንገንባ ።ከዚያም ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነ ለማየት እንመረምራለን ።**
- ከልጅዎ ጋር በመሆን እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ወረቀት ላይ አንድ መዋቅር ይገንቡ ።
- ከዚያ በኋላ ፣ አወቃቀሩ ይወድቅ እንደሆነ ለማየት ልጅዎ ወረቀቱን በቀስታ ወደ ፊት እና ወደ ኋላ እንዲንሸራተት ይፍቀዱለት።  ልጅዎ ፣ አወቃቀሩ እንዲወድቅ በምን ያህል ፍጥነት ማንሸራተት እንዳለበት ለማየት ይችል ዘንድ በፍጥነት ማንሸራተት ይችላል።
- ይጠይቁ, **ሕንፃችን እንዲወድቅ ወረቀቱን በምን ያህል ፍጥነት ማንቀሳቀስ ነበረብህ? እንዳይወድቅ እንዴት ጠንካራ ልናደርገው እንችላለን ብለህ ታስባለህ?**

## እራሱን የቻለ ትምህርት : **Lou Lou /**ሉ ሉ እና ሕፃኑ ድብ




**ቁሳቁሶች**: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*

- ይጠይቁ, **(Lou Lou)ሉ ሉ የሕፃን ድብን ገንፎን ስትበላበት ምን ተሰማት?  ሕፃኑ ድብ ሉ ሉ ገንፎውን ስትበላበት ምን ተሰማው?**
- ይህን ይበሉ, **የተለያየ ስሜት ነበራቸው። ሕፃኑ ድብ አዝኖ ነበር እና (Lou Lou) ሉ ሉ ደግሞ በጣም ተደስታ ነበር :: ህጻኑ ድብ እና (Lou Lou) ሉ ሉ በዚህ ጉዳይ ላይ ሲናገሩ ለማሳየት ስዕል መሳል ትችላለህ ።**
- ከዚያ, በኋላ, **ስለ ስዕልህ ንገረኝ ። ህፃኑ ድብ ለ(Lou Lou) ሉ ሉ እንዳዘነ ሲነግራትምን ምን የምትለው ይመስልሃል?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሐሙስ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 1  ቀን4

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ግብ ምንድን ነው?

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, ወረቀት**

- ይህን ይበሉ, **ግብ ማለት ለማግኘት የሚፈልጉትን ነገር እና ለማግኘት ወይንም ለማድረግ የሚሞክሩት ማለት ነው፡ ፡** እርስዎ ወይም ቤተሰብዎ ያለዉን ግብ ያጋሩ ።
- ይህን ይበሉ, **ግብ  እናስቀምጥ ።  ዛሬ እንዲከናወን የምንፈልገው ነገር ምንድነው?**
- ልጅዎ ስለ ግቡ እንዲጽፍ እና እንዲስል ይርዱት ።
- በቀኑ መጨረሻ ላይ ግቡን ካሳካችሁ ፣አብራችሁ ማረጋገጥ ትችላላችሁ ።

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የግንባታ ተሽከርካሪዎች

**ቁሳቁሶች: ከላሮች, የግንባታ ተሽከርካሪዎች ጆርናል ገጽ**




- ከልጅዎ ጋር ስለ የግንባታ ተሽከርካሪዎች ዓይነቶች እና ስለ ሥራዎቻቸው ይነጋገሩ።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ስለሚወደው የግንባታ ተሽከርካሪ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ለምን እንዲህ ዓይነቱን ተሽከርካሪ መረጥክ?  ያንን ተሽከርካሪ መንዳት ምን ሊመስል ይችላል ብለው ታስባለህ?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ስም: _________________

ያንተ ተወዳጅ የግንባታ ተሽከርካሪ ምንድነው?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# አርብ




## STEM: ቁጠር እና ተንቀሳቀስ

- የተለያዩ የግንባታ እንቅስቃሴዎችን በሚያደርጉበት ወቅት ከልጅዎ ጋር እስከ 15 ድረስ በመቁጠር ይለማመዱ ። ይህን ይባሉ, **እስከ 15 ድረስ እንቆጥራለን እና በተለያዩ መንገዶች እንንቀሳቀስ! እንደ ቆፋሪ ፣ቁፈራን በማስመሰል እስከ 15 ድረስ መቁጠር እንችላለን ። 1 ፣ 2 ፣ ... 15! ጥሩ ቁፋሮ!**
- ሌሎች እንቅስቃሴዎችን እንደ ስዕል መሳል ፣ ንድፍ መንደፍ ፣ መጥረግ ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ይሞክሩ ። ልጅዎ እንቅስቃሴዎችን እንዲጠቅስ / ሀሳብ እንዲሰጥ ያድርጉ ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ ቅርፅ ማስታወስ

**ቁሳቁሶች**: ከ 1 ኛ ሳምንት 1 ቀን ጀምሮ ወደ ካርዶች የተቆረጡ ቅርፃች

- ከልጅዎ ጋር 3 ጥንድ ቅርጾችን ይምረጡ ። ይሰይሟቸው ፣ ከዚያ ፊታቸውን ወደታች ያዙሯቸው።
- ይህን ይበሉ, **ማዛመድ ይችሉ ዘንድ እና ተመሳሳይ ቅርፅ ማግኘት ይችሉ እንደሆነ ለማየት 2 ካርዶችን ያዙሩ።**
- ተዛማጅ ሆነው ካገኙ ጥንዶቹን ማንሳት ይችላሉ ። ካልተዛመዱ ፣ ችግር የለውም። ይገልብጧቸውና እና እንደገና ሊሞክሯቸው ይችላሉ ።
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ጨዋታውን እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ።




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# አርብ



## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የታሪክ ግብ


**ቁሳቁሶች**: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*



- ይህን ይበሉ, **ትናንትና ለዛሬያችን ግብ አዘጋጅተን ነበር።**
- ይጠይቁ, **ግብ ምንድን ነዉ? ግብ ማለት ለማግኘት የሚፈልጉትን ነገር እና ለማግኘት ወይንም ለማድረግ የሚሞክሩት ነው**
- ይህን ይበሉ, **በታሪኩ ውስጥ, ገፀ ባህሪያት ግቦች ሊኖራቸው ይችላል::**
- ይህን ይባሉ, **ከዚህ መጽሐፍ ላይ አነበባለሁ እናም ግቡ ምን እንደሆነ እንድትነግረኝ እፈልጋለሁ ።** አንብብ ገፅ.6-9 *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ* . ይጠይቁ, **(Lou Lou) የሉ ሉ ግብ ምን ነበር? አዎ ፣ (Lou Lou) ሉ ሉ ገንፎውን መብላት ፈለገ ።**

## Read: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*

**ቁሳቁሶች**: *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*




- ከልጆ ጋር, ያንብቡ *(Just Right: Lou, Lou and the Bears) ጀስት ራይት: ሉ ፣ ሉ እና ድቦቹ*
- በኋላ, ይጠይቁ, **በኋላ ፣ ይጠይቁ ፣ በታሪኩ ውስጥ የሉ ሉ (Lou Lou) ግብ ምንድን ነበር?**
- **(Lou Lou) ሉ ሉ መብላት ፣ ማንበብ እና መተኛት ፈለገ።**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሳምንት 2


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2 አጠቃላይ እይታ


## የግንባታ ሰራተኞች እና መሳሪያዎች



### በዚህ ሳምንት ልጅዎ ይህንን ይማራል:

ስለ የግንባታ ሠራተኞች እና ስለ መሣሪያዎቻቸው እና ማሽኖቻቸው ይማሩ ::

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



**ንድፍ**

በወረቀት ላይ የተሳለ የሕንፃ ዕቅድ



**ግንባታ**

እንደ ቤት እና መንገዶች ያሉ ነገሮችን እንዴት እንደምንገነባ



**መሣሪያ**

በእጅዎ የሚይዙት ነገር እና ስራ ለመስራት የሚጠቀሙበት


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

በዚህ ሳምንት ስለ የግንባታ ሠራተኞች እና ስለ መሣሪያዎቻቸው እና ማሽኖቻቸው ይማራሉ ። የግንባታ ሠራተኛ ቢሆኑ ኖሮ ምን ያደርጉ ነበር?

አስብበት!


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሰኞ



## **STEM:** እንቁጠር !

- ይህን ይበሉ, **የሞኝ /ሲሊ ድምፆችን በመጠቀም እስከ 15 ድረስ እንቁጠር ። በሮቦት ድምጽ እንቁጠር ። የሮቦት ድምፅ ምን ይመስላል ብለህ ታስባላህ?**
- 1-2 ተጨማሪ ጊዜዎችን ይቁጠሩ ። ልጅዎ የተለያዩ ድምጾችን ለምሳሌ እንደ ፣ ሹክሹክታ ወይም ሞንስተር /ጭራቅ ያሉትን እንዲመርጥ ይፍቀዱለት።

## እራሱን የቻለ ትምህርት : ንድፎችን መንደፍ

- ይጠይቁ, **ንድፍ ምን እንደ ሆነ ታስታውሳለህ? አዎን ፣ ንድፍ የሕንፃ ዕቅድ ወይም ዲዛይን ነው ።**
- **በቤታችን ውስጥ የአንዱን ክፍል ንድፍ ወይም ዲዛይን ማውጣት ትችላለህ።**
- ልጅዎ የመረጠውን ክፍል ንድፍ እራሱን ችሎ እንዲያወጣ ያድርጉት ።
- በኋላ, ይህን ይበሉ, **ስለ ንድፍህ ንገረኝ?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሰኞ


PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2  ቀን6

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ:  ሲላብልስ ማደባለቅ

- ይህን ይበሉ, **ሲላብልስ በአንድ ቃል ውስጥ የሚገኙ ምቶች ናቸው ።  ባለ ሁለት ሲላብልስ ቃላት ባለ ሁለት ምት ናቸው። እንደ ውሃ ያሉ ቃላቶች ሁለት ምቶች ያላቸው ባለ ሁለት ሲላብልስ ናቸው - wa-ter. ከእኔ ጋር ምቾቹን ያጨበጭቡ: wa-ter.**
- ይህን ይበሉ, **ሲላብልስን Blend/ብሌንድ እናድርግ! Blend/ብሌንድ ማለት አንድ ላይ ማደባለቅ ማለት ነው።**
- **ሁለት ሲላብልስን እላለሁ ።  አንድ ላይ ሰብስባቸው እና ቃሉን ንገረኝ ። Pop** (ቆም በል) **corn. Pop-corn. ቃሉ ምንድነው? Popcorn! / ፈንድሻ !**
- ብዙ ማወደሶን / ውዳሴ መስጠትዎን ያስታውሱ! **Good job! /ምርጥ ስራ!**
- ለblueprint (blue-print) እና ለ building (build-ing) ይድገሙት።

## ኣንብብ: ***(Go Outside and Play)*** *ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ*

ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ በፌሊሺያ ትሩንግ




**ቁሳቁሶች**: *(Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ*

- በጋራ, ያንብቡ *(Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ.* ካነበቡ በኋላ, ልጅዎ በመጽሐፉ ውስጥ የሚወደውን ገጽ እንዲመርጥ ያበረታቱት ። ይጠይቁ, **ይህ ለምን ነው ያንተ ተወዳጅ ገጽ የሆነው?  በዚህ ገጽ ላይ ምን ዓይነት ቅርጾችን ታስተውላለህ?**
- በጋራ, እነዚያን ቅርጾች በቤትዎ ውስጥ ወይም ውጭ ለማግኘት ይሞክሩ ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ማክሰኞ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን7


## STEM: መገንባት እችላለሁ

**ቁሳቁሶች: እንደ የጭማቂ መያዣ ሳጥኖች ወይም እንደ ፕላስቲክ ኮንቴይነሮች ያሉ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ቁሳቁሶችን ያጽዱ**

- ይህን ይበሉ, **የሆነ ነገር ልገነባ ነው ። ከዚያ አንተም ለመገንባት እንድትሞክር እፈልጋለሁ ።**
- አንድ ቀላል ነገር ይገንቡ እና እንዴት እንደገነቡት ይግለጹ። ይበሉ ፣ **ይህንን እዚህ እዚኛው ላይ አስቀመጥኩት ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ የእርሶን አስመስሎ እንዲቀዳና እና እንዲገነባ ያድርጉ።
- እርዳታ ከፈለገ ችግር የለውም ፣ ፍንጭ መስጠት ወይም አብረው መገንባት ይችላሉ ።
- ከዚያ ፣ ሚናዎችን ይቀይሩ። ልጅዎ እርስዎ ደግሞ መቅዳት እንዲችሉ አንድ ነገር ሊገነባ ይችላል።

## እራሱን የቻለ ትምህርት : የግንባታ ተሽከርካሪ እንቆቅልሾች / ፖዝል

**ቁሳቁሶች: የግንባታ ተሽከርካሪ እንቆቅልሾች / ፖዝል, ከለሮች, መቀሶች, *አማራጭ - ቁርጥራጮቹን ከመቁረጥዎ በፊት እንቆቅልሹን እንደ ሲራል / ሳጥን ያሉ ካርቶኖች ላይ ያጣብቁ***



- ይህን ይበሉ, **የግንባታ እንቆቅልሽ / ፖዝል ልት ሰራ ነው ። በመጀመሪያ ስዕሉን ቀለም መቀባት ትችላለህ ።**
- ልጅዎ ስዕሉን ካቀለመ በኋላ ቁርጥራጮቹን ይቁረጡ።
- ልጅዎ እንቆቅልሹን በተናጥል እንዲያጠናቅቅ ያድርጉ ፣ አስፈላጊ ከሆነም ይርዱት ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ማክሰኞ




## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ተከተለኝ

- ይህን ይበሉ, **እስቲ እንጫወት ተከተለኝ ። እኔ ያልኩትን አዳምጥና ከዚያ አድርግ።**
- ለልጅዎ ሁለት-ደረጃ ትዕዛዞችን ይስጡት፡ ወደ ላይ ዘልለው ከዚያ ጣቶችዎን ያስጩሁ፣ እጆችዎን ያጨበጭቡ እና ከዚያ አፍንጫዎን ይንኩ ፣ ዊግል / ይወዛወዙ እና ከዚያ ፈገግ ይበሉ ፣ ወዘተ።
- ልጅዎ ትዛዦችን እንዲሰጥዋ ሚናዎችን ተቀያየሩ ።


## የፅሁፍ ሃሳብ፡ ባክ ሆ / ትራክተር

**ቁሳቁሶች**: **ከለር, ባክ ሆ/ትራክተር ጆርናል ገጽ**





- ከልጅዎ ጋር የግንባታ ሰራተኞች ለምን ባክ ሆ/ ትራክንተር እንደሚጠቀሙ ይነጋገሩ - ጉድጓዶችን ለመቆፈር ፣ የተወሰነ ቁሳቁሶችን ለመሸከም ፣ በመሰባበር ለመርዳት እና መንገዶችን ለማስተካከል ይረዳል ። በስልክ ወይም በታብሌት ላይ በስራ ላይ ያሉ ባክ ሆ / ትራክተሮችን ፎቶግራፎችን ማየት ይችላሉ ።
- ልጅዎ ባክ ሆ / ትራክተሮች ለምን ጥቅም ላይ እንደሚውል ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለፃፍከው ነገር ንገረኝ ። የግንባታ ሠራተኛው ባክ ሆ / ትራክተሩን ምንን ለመገንባት ተጠቀመበት?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ስም: ________________

የግንባታ ሠራተኞችን ባክ ሆ / ትራክተርን ምንን ለመገንባት ይጠቀሙበታል?



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን8

## STEM: ነጥቦቹን ማወዳደር


**ቁሳቁሶች**: [ነጥብ ካርዶች 0-3]() **በተናጠል ካርዶችን መቁረጥ**



- ለልጅዎ 2 ካርዶችን ያሳዩ። ይጠይቁ፣ **ብዙ ነጥቦችን ወደያዘው አመልክት /ጠቁም።** ሳይቆጥሩ ለመጠቆም መሞከር አለባቸው ። ለማጣራት ቢቆጥሩ ችግር የለውም ።
- 1-2 ተጨማሪ ጥንድ ካርዶችን አሳያቸው እና የትኛው ትንሽ ወይም ብዙ ነጥቦች እንዳሉት ይጠይቁት ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት መሳሪያዎችን ቀለም መቀባት

**ቁሳቁሶች**: [መሳሪያዎች ቀለም መቀቢያ ገጾች](), **ከለሮች**



- ከልጅዎ ጋር ስለ መሳሪያዎቹ እና ስለሚሰሩት ነገር ይነጋገሩ።
- ልጅዎ እራሱን ችሎ መሣሪያዎቹን ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **የትኛውን መሣሪያ መጠቀም ትፈልጋለህ? ለምን?**
- ስዕሎችን በዚህ ሳምንት ለሌሎች እንቅስቃሴዎች እንዲጠቀሙበት ያስቀምጡ ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2  ቀን8


## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ግቡ ምንድን ነው?

**ቁሳቁሶች**: (Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ

- ይጠይቁ, **ግብ ምንድን ነው? ግብ የምንፈልገው ነገር ነው እናም ለማግኘት ወይም ለማድረግ የምንሞክረው ነው ፡፡**
- ይህን ይበሉ, **ከዚህ መጽሐፍ አንድ ገጽ አነባለሁ ፡፡  ግቡ ምን እንደሆነ ትነግረኛለህ ፡፡**
- አንብብ ገፅ.10-11 የ *(Go Outside and Play)* ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ፡፡  ይጠይቁ, **የአሌክ (Alex's) ግብ ምን ነበር?**  ለአፍታ አቁም  **አዎ ቅርጾችን ለማግኘት ነው፡፡**

## Read: (Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ

ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ በፌሊሺያ ትሩንግ




**ቁሳቁሶች**: (Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ

- በጋራ, ያንብቡ (Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ፡፡
- ከዚያ, ይህን ይበሉ, **አንድ ቅርጽ እጠራለሁ አንተም ቅርፁን ፈልገህ ታገኛለህ፡፡**
- ሚናዎችን ይቀይሩ እርሶ ቅርፁን ፈልገው እንዲያገኙ ልጅዎ ቅርጽ እንዲጠራ ያድርጉ ፡፡


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የአፕል ትሪ ተቋም ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ፡፡.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2  ቀን8

## እንቀሳቀስ፡ ፍሪዝ ዳንስ

**ቁሳቁሶች: ሙዚቃ**


- ይህን ይባሉ, **ፍሪዝ ዳንስ እንጫወት ። ሙዚቃው እስከተጫወተ ድረስ እንደንሳለን ። ልክ ሙዚቃው እንዳቆመ እኛም እናቆማለን / ፍሪዝ እናደርጋለን !**
- ጥቂት ዙሮችን ይጫወቱ ።  ልጅዎ የሙዚቃውን ኃላፊነት እንዲይዝ ሚናዎችን መቀየር ይችላሉ።  ወይም ዘፈን መዝፈን እና መቼ ማቆም እንዳለባቸው መምረጥ ይችላሉ ።

## በጋራ መማር፡ ያየነውን ዕንሳል


**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ስለሮች ወይም ውሃማ ቀለም ያለው ፖሌት, አማራጭ - ቴፕ**

- ከልጅዎ ጋር በመስኮት ይመልከቱ እና ስለምታዩት ነገር ተነጋገረ ።
- ይህን ይበሉ, **በመስኮቱ ስለምናየው ነገር ለመሳል በጋራ እንሥራ ።**
- በአንድ ወረቀት ላይ አንድ ስዕል ይሳሉ ወይም ሁለት ወረቀቶችን በአንድ ላይ በማጣበቅ አንድ ትልቅ ስዕል ይስሩ ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.




© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.



# መዶሻ


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.



መፍቻ


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሀሙስ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን9

## STEM: ለምንድን ነው ጣሪያ የሚያስፈልግዎ?

**ቁሳቁሶች: ኩባያ ውሃ ፣ ሳህን ፣ ካርቶን ለምሳሌ. አንድ የሳጥን ቁርጥራጭ ወይም ፎይል**

- ይጠይቁ, **ለህንፃዎች ጣሪያ መኖሩ ለምን አስፈላጊ ነው ብለው ታስባለህ?**
- ይህን ይበሉ, **ጣራ ባይኖረን እና ዝናብ መዝነብ ቢጀምር ምን ሊሆን እንደሚችል ለማየት አንድ ሙከራ እናድርግ ።**
- ትንሽ ጣራ ያለው ድንኳን ለመሥራት ልጅዎ ካርቶኑንን ሳህኑ ላይ እንዲያጥፍ ይፍቀዱለት ። ከዛም ጣቶቹን በመጠቀም ውሃውን በጣሪያው ላይ ይርጭ ። በጣሪያው ላይ ስላየው ነገር ይናገሩ። ከዚያ ጣሪያውን ያንሱ እና ሳህኑን ይመልከቱ፣ ደረቅ መሆን አለበት።
- ጣሪያው ሳይኖር በሳህኑ ላይ ውሃ ይርጩ እናም ሳህኑ እንደረጠበ ወይንም ደርቅ እንደሆነ ይናገሩ ። ይጠይቁ ፣ **በሕንፃ ላይ ጣሪያ መኖሩ ምንድነው አስፈላጊነቱ ?**

## እራሱን የቻለ ትምህርት : እኔን በመሆኔ ደስተኛ ነኝ

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ስለሮች**

- ስለእነርሱ ልዩ ስለሆኑ ነገሮች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ። ይጠይቁ ፣ **እራስህን በመሆንህ ልዩ እና ደስተኛ የሚያደርግህ ምንድን ነው?**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ እራሱን ልዩ እና ደስተኛ ስለሚያደርጉት ነገሮች እንዲጽፍ እና እንዲስል ያድርጉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ፃፍከው ነገር ንገረኝ! በጣም ልዩ ሰዉ ነዉ - አንተ!**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሐሙስ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2  ቀን9


## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ማደባለቅ ባለ ሁለት–ሲላብል ቃላት

- ይህን ይበሉ, **አንድ ቃል ለመመስረት ሁለት ሲላብል እናደባልቅ !**
- **ሁለት ሲላብል እጠራለሁ :: በአንድ ላይ አድርግና ቃሉን ንገረኝ፡፡  Ham** ( ላፍታ ቆም በል) **mer.  Ham-mer. ቃሉ ምንድን ነው?**
- ይድገሙ ለ tractor / ትራክተር (trac-tor) እና highway / ሀይዌይ (high-way). ልጅዎ ቃሉን እንዲነግሩት ከፈለገ ችግር የለውም፡፡  አሁንም እየተማሩ ነው ::

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ መሳሪያ

**ቁሳቁሶች: ስለሮች, መሳሪያዎች ጆርናል**

- ከልጅዎ ጋር ስለ የተለያዩ መሳሪያዎች እና ምን ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይነጋገሩ፡፡
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ስለሚወደው መሣሪያ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ::
- በኋላ, ይጠይቁ, **ለምን እንዲህ ዓይነቱን መሣሪያ መረጥክ?  በመሳሪያዎ ምን ትገነባበታላህ?**


ስም: ________________
የእርሶ ተወዳጅ መሳሪያ ምንድን ነው?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የአፕል ትሪ ተቋም ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ፡፡.

ስም: _________________

የእርሶ ተወዳጅ መሳሪያ ምንድን ነው?



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# አርብ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2  ቀን10

## STEM: ቅርፁን ፈልግ


**ቁሳቁሶች: በሳምንት 1  ቀን 1 ወደ ካርድነት የተቆረጡ [ቅርፆች](#)**



- አንዱን የቅርጾችን ብሰብ ይያዙ እና ለልጅዎ ሌላኛውን የካርድ ስብስብ ይስጡት።
- ይህን ይበሉ, **እንድ ቅርጽ እጠራለሁ እናም አንተ ቅርጹን እንድታሳየኝ እፈልጋለሁ። Rectangle / አራት መአዘን!**
- ለሌሎቹም ቅርጾች ይድገሙ። ከእርስዎ ስብስብ ውስጥ አንድ ቅርጽ በማሳየት ልጅዎን መርዳት ቢያስፈልግዎት፣ ችግር የለውም ነው ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት : Making Shapes

**ቁሳቁሶች: [ቅርፆች](#), የመጫወቻ ጭቃ, [የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት](#)**



የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ።
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ። ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ።
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ።
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ።
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ። አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት።

- ከልጆ ጋር, 3-4 ቅርጾችን ይሰይሙና ጎኖቹን ይቆጠሩ ።
- ይህን ይበሉ, **ይህ ካሬ ነው ፣ ጎኖቹን እንቁጠራቸው ። 1, 2, 3, 4. አራት ጎኖች አሉት ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ የመጫወቻ ሊጡን በመጠቀም ቅርጾችን ለመሥራት እንዲሞክር ያድርጉ። ቅርጾቹን የማያስመስሉ ከሆነ ችግር የለም።  እየተለማመደ ነው ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# አርብ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 2 ቀን10


## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የእርስዎ ችግር እና ግብ

**ቁሳቁሶች**: **ወረቀት, ስለሮች**

- ይህን ይበሉ, **ስለ ችግሮች እና ግቦች እየተማርን ነበር ።**
- ይጠይቁ, **አንተ ያለብህ ችግር ምንድን ነው?**
- በኋላ, ይጠይቁ, **ለዚያ ችግር ግብህ ምንድነው?**
- ልጅዎ ለዚያ ችግር ያስቀመጠውን ግብ እንዲጽፍ ያበረታቱት ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ፃፍከዉ ነገር ንገረኝ።**

## አንብብ፡ ***(Go Outside and Play)*** *ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ*

ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ በፌሊሺያ ትሩንግ




**ቁሳቁሶች**: *(Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ*

- በጋራ, አንብቡ *(Go Outside and Play) ውጭ ይውጡ እና ይጫወቱ።*
- ካነበባችሁ በኋላ, በዙሪያቸው ስላሉ ቅርጾች ለልጅዎ ፍንጭ በመስጠት እናም እቃውን መገመት ይችሉ እንደሆነ ይመልከቱ ። ይህን ማለት ይችላሉ፣ **ጊዜን የሚገልጽ እንደ ክብ ቅርጽ ያለው ነገር አየሁ ።**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሳምንት 3


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 አጠቃላይ እይታ

## የመንገድ ግንባታ ሠራተኛ



### በዚህ ሳምንት ልጆ ይህንን ይማራል :

ስለ መንገዶች ፣ መወጣጫዎች እና የመዝናኛ ፓርኮች ይማሩ ።

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



## የመዝናኛ ፓርኮች

ጨዋታዎች እና የሚነዱ ነገሮች ያሉት ትልቅ ቦታ



## መወጣጫ

ሁለት ከፍታዎችን የሚያገናኝ ነገር



## መንገድ

ለመንዳት እና ለመራመድ የተሠራ ጠንካራ ገጽ



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

አስብበት!

በዚህ ሳምንት ስለ መንገዶች ፣ ስለ መወጣጫዎች እና ስለ መናፈሻ ፓርኮች ይማራሉ ።
ፓኬቱን ከመጀመርዎ በፊት ምን ዓይነት የመናፈሻ ፓርክ እንደሚገነቡ ይጻፉ እና ይሳሉ ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሰኞ




## STEM: እናወዳድር

**ቁሳቁሶች: የቤት ውስጥ አቃዎች እንደ ከለሮች ወይም ጠጠሮች**

- እያንዳንዳቸው 2 ከለሮችን የያዙ 2 የከለር ቡድኖችን ይስሩ ፡፡
- ይጠይቁ, **እነዚህ ቡድኖች ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ከለሮችን ይዘዋል ወይንስ አንዱ ቡድን ተጨማሪ ከለር ይዟል?** ልጅዎ ሳይቆጥር ለመመለስ እንዲሞክር ያበረታቱት ፣ ግን ለማጣራት ቢቆጥር ችግር የለውም፡፡
- ለማወዳደር ቀላል የሆኑ 1-2 ተጨማሪ የከለሮች ቡድኖችን ያሳዩት (በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ ከ 5 እንዳይበልጡ ለምሳሌ 5 ክሬኖች እና 1 ክሬን) ፡፡  የትኛው ቡድን ያነሰ ወይም የበለጠ ከለሮች እንዳሉት ወይም ተመሳሳይ መጠን ካላቸው ይጠይቁ፡፡

## እራሱን የቻለ ትምህርት: የህንፃ የግንባታ ደረጃዎች

**ቁሳቁሶች**: [የህንፃ የግንባታ ደረጃዎች](), **ከለሮች**




- ከልጅዎ ጋር ስለ የሕንፃ የግንባታ ደረጃዎች ይነጋገሩ፡፡  ይህን ይበሉ ፣ **በመጀመሪያ ንድፍ ወይም እቅድ ይሳሉ ፡፡ በሁለተኛ ደረጃ እነሱ የሚገነቡበትን መሬት ያፀዳሉ ፡፡ ሦስተኛ ፣ ሁሉንም ምርካቸውን በአንድ ላይ ያሰባስባሉ ፡፡ በመጨረሻም በተጠረገው የግንባታ ቦታ ላይ መገንባት ይጀምራሉ ፡፡**
- ልጅዎ እያንዳንዱን ሥዕል ራሱን ችሎ ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ፡፡
- ከዚያ ፣ልጅዎ እራሱን ችሎ የግንባታ ደረጃዎቹን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይችላል፡፡
- ከዚያ, በነዚህ የግንባታ ደረጃዎች ላይ አብረው ይሳተፉ፡፡ ይጠይቁ, **የትኛው ቀድሞ ይመጣል?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የአፕል ትሪ ተቋም ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ፡፡.

# ሰኞ


PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን11

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ባለሶስት ደረጃ ትዕዛዞች

- ይህን ይበሉ, **ተከተለኝ የተሰኘውን ጨዋታ እንጫወት፣ በዚህ ጨዋታ ላይ በጣም ጥሩ እየሆንክ ነው የመጣኸው! ሶስት ትዕዛዞችን እስጥሀለው ። ስለዚህ በጥሞና አዳምጥ!**
- ለልጅዎ ባለሶስት-ደረጃ ትዕዛዞችን ይስጡት: አፍንጫህን ንካ ፣ ጣቶችህን አስጨህ ፣ ከዚያ እጆችህን አጨብጭብ ወይም ጭንቅላትህን ነካካ ፣ ትከሻህን ነካካ ፣ ከዚያ ጉልበትህን ነካካ ።
- ልጅዎ ትዕዛዞችን እንዲሰጥ ሚናዎችን ይቀያየሩ።

## አንብብ፡ ***(Tying My Shoes)*** *ጫማዎቼን ማሰር*


ጫማዎቼን ማሰር ፅሁፍ በጁሊ ፎውለር ምስል በኬነዲ ኋይት





**ቁሳቁሶች**: *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር*

- ከልጆ ጋር, ያንብቡ *(Tying My Shoes)* *ጫማዎቼን ማሰር።*
- ይህን ይበሉ, **Bobby /ቦቢ ጫማዎቹን ለማሰር የተቻለውን ሁሉ ጥረት አድርጓል ። አንተስ ፣ የተቻለህን ሁሉ በማድረግ የሞከርከው አዲስ ነገር ምንድነው? ስታደርገው ምን ተሰማህ?**



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.





ንድፍ መሣል



ቁሳቁሶችን ማሰባሰብ



መሬቱን ማፅዳት



የግንባታ ሳይት/ ስፍራ ላይ መገንባት


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ማክሰኞ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን12

## STEM: የተነጠፈ እና ያልተነጠፈ

**ቁሳቁሶች: ጥቂት ጠጠሮች ፣ ዐለቶች ፣ ወይም የሚያንገጫግጭ ነገር ፣ እና ትንሽ ኳስ ወይም እንደ ኳስ የተጠቀለለ ወረቀት**

- ይጠይቁ, **መንገዶች ለምን መጠረግ ወይም ለስላሳ መደረግ አለባቸው ብለህ ታስባለህ? ለስላሳ ካልሆኑ ምን ይከሰታል?**
- **እስቲ ይህ ኳስ ጎማ ነው ብለን እናስብ እና የትኛው መንገድ በተሻለ እንዲሽከረከር ያደርገዋል ።** ልጁ ኳሱን በጠጠር “መንገድ” ላይ ወይም እንደ ወለሉ ለስላሳ በሆነ ቦታ ላይ እንዴት እንደሚሽከረከር ማወዳደር ይችላል።

## እራሱን የቻለ ትምህርት; መንገዶች እና አውራ ጎዳናዎችን መሳል

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ከለሮች**

- ከልጅዎ ጋር የመንገድ እና የአውራ ጎዳናዎችን ስዕሎችን በስልክ ወይም በታብሌት ላይ ይመልከቱ ። ልጅዎ ያስተዋለውን እንዲገልጽ ይጠይቁ ።
- ልጅዎ የራሱን መንገድ ወይም አውራ ጎዳና እራሱን ችሎ እንዲስል እና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ መንገዱ ወይም ስለ አውራ ጎዳናው ንገረኝ ። በዚህ ላይ የሚነዱት ምን ዓይነት ተሽከርካሪዎች ናቸው?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.


# ማክሰኞ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን12

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: ችግሩ ምንድን ነው?

**ቁሳቁሶች**: *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር*

- ይህን ይበሉ, **የዚህን መጽሐፍ ጥቂት ገጾች አነባለሁ ። በታሪኩ ውስጥ ስላለው ችግር እንድታስብ እፈልጋለሁ ። ችግሩ ምንድነው?** ለአፍታ ቆም ይበሉ **አዎ ፣ የተሳሳተ ነገር አለ።**
- አንብብ ገፅ. 8-9 of *(Tying My Shoes)* ***ጫማዎቼን ማሰር*** ።
- ይጠይቁ, **ችግሩ ምንድን ነው?** ለአፍታ ቆም ይበሉ. **Bobby /ቦቢ ቀለበቶችን መሥራት አልቻለም ።**




ጫማዎቼን ማሰር ፅሁፍ በጁሊ ፎውለር ምስል በኬነዲ ኋይት

## የፅሁፍ ሃሳብ: የመንገድ ግንባታ ሰራተኞች

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የመንገድ ግንባታ ሰራተኞች ጆርናል ገፅ**

- ከልጅዎ ጋር ስለ የመንገድ ግንባታ ሰራተኞች እና መንገዶችን ለመገንባት ሰራተኞቹ ምን እንደሚያደርጉ ይነጋገሩ ። የመንገድ ግንባታ ሰራተኞች የሚያሳዩ ሥዕሎችን በስልክዎ ወይም በታብሌትዎ ላይ ማየት ይችላሉ ።
- ልጅዎ የመንገድ ግንባታ ሰራተኛ ቢሆን ኖሮ የቀን ውሎው ምን ሊመስል እንደሚችል ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **እንደ የመንገድ ግንባታ ሰራተኛ ስለነበረህ የቀን ውሎህ ንገረኝ ። መጀመሪያ ምን ታደርጋለህ?**


ስም: ________________

የመንገድ ግንባታ ሰራተኛ ብትሆን ኖሮ የቀን ውሎህ ምን ሊመስል ይችላል?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ስም: ________________

የመንገድ ግንባታ ሰራተኛ ብትሆን ኖሮ የቀን ውሎህ ምን ሊመስል ይችላል?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን13


## STEM: ቁጠር እና ተንቀሳቀስ

- የተለያዩ የግንባታ እንቅስቃሴዎችን በሚያደርጉበት ጊዜ ከልጅዎ ጋር እስከ 15 ድረስ መቁጠርን ይለማመዱ። ይህን ይበሉ, **እስከ 15 ድረስ እንቁጠር እና በተለያዩ መንገዶች እንቀሳቀስ! እንደ ሲሚንቶ አቡኪ በማስመሰል እስከ 15 ድረስ መቁጠር እንችላለን ። 1 ፣ 2 ፣ ... 15! ጥሩ ድብልቅ!**
- ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ይሞክሩ ፣ ለምሳሌ ቁሳቁሶችን መጫን ፣ ቆፍረው ከዚያ ቆሻሻን መጣል ፣ ወዘተ። ልጅዎ እንቅስቃሴዎችን እንዲጠቁም/ሀሳብ እንዲሰጥ ይፍቀዱለት።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ለBobby/ቦቢ ደብዳቤ

**ቁሳቁሶች**: *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር*, **ወረቀት, ከለሮች**

- ከልጆ ጋር, ስለ መፅሀፉ ይነጋገሩ, *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር.* ይህን ይበሉ, **መጀመሪያ ላይ Bobby / ቦቢ ጫማውን ማሰር ሲያቅተው ተበሳጨ። የተቻለውን ሁሉ ጥረት እንዲያደርግ ለማበረታታት ለቦቢ ደብዳቤ መጻፍ ትችላለህ ።**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ደብዳቤውን እንዲጽፍ እና እንዲስል ያድርጉ።
- ከዚያ, ይህን ይጠይቁ, **ለቦቢ/Bobby ምን ጻፍክ?**




ጫማዎቼን ማሰር ፅሁፍ በጁሊ ፎውለር ምስል በኬነዲ ኋይት


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን13


## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ባለ ሁለት ሲላብል ቃላትን ማደባለቅ ክለሳ

- ይህን ይበሉ, **አንድ ቃል ለመመሰረት ሁለት ሲላብል ማደባለቅ!**
- **ሁለት ሲላብል እነግርሀለው ፡፡ አንድ ላይ ሰብስባቸው እና ቃሉን ንገረኝ ፡፡ Puz** (ለአፍታ ቆም ይበሉ) **zle. Puz-zle. ቃሉ ምንድን ነው?**
- ለ feeling /ስሜት(feel-ing) እና problem/ ችግር (prob-lem). ልጅዎ የእርስዎ ድጋፍ ከፈለገ ችግር የለውም፡፡ አሁንም እየተማረ ስለሆነ ነው ፡፡

## ኣንብብ: ***(Tying My Shoes)*** *ጫማዎቼን ማሰር*

**ቁሳቁሶች**: *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር*

- ከልጆ ጋር ይነጋገሩ, አንብብ *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር ፡፡*
- ከዚያ, አሳይ ገፅ. 8-9. ይህን , **Bobby /ቦቢ መጀመሪያ ጫማውን ማሰር ሲያቅተው ተበሳጨ ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ነገሮች አስቸጋሪ በሚሆኑበት ጊዜ ሁላችንም እንበሳጫለን ፡፡**
- **ብስጭት በሚስማህ ጊዜ ምን ማድረግ ትችላለህ?**




ጫማዎቼን ማሰር ፅሁፍ በጁሊ ፎውለር ምስል በኬነዲ ኋይት


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የአፕል ትሪ ተቋም ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ፡፡.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3  ቀን13

## እንቅሳቀስ፡ እንደ መሪው ይቁጠሩ

- ይህን ይበሉ, **እስከ 15 እንቁጠር!  ከመካከላችን አንዱ መሪ ይሆናል እና እየቆጠርን ሌላኛው ሰው የመሪውን የዳንስ እንቅስቃሴ ኮፒ ያደርጋል /ይቀዳል ።**
- ቢያንስ 2 ጊዜ ይቁጠሩ እና ተራ በተራ ይምሩ ።

## በጋራ መማር፡ ርዝመትን ማሰስ

**ቁሳቁሶች: የቤት ውስጥ ቍሳቁሶች እንደ ከለሮች, ወረቀት ክሊፕስ, ማንኪያ**

- ይህን ይበሉ, **ርዝመቱን ወይም ይህ ነገሮርች ምን ያህል እንደሆኑ እንለካ ።ግንበኞች አንድን ነገር  ከመቁረጣቸው በፊት ርዝመት ማወቅ በህንፃቸው ውስጥ ምን እንደሚመጥን ማወቅ አለባቸው ።  ርዝመትን ለመለካት እንለማመድ ።**
- እንደ ከለሮች ወይም የወረቀት ክሊፖች ያሉ ነገሮችን በመጠቀም የተለያዩ ዕቃዎችን መለካት ይለማመዱ ።  ለምሳሌ ፣ይህን ይበሉ ፣ **እጃችን ምን ያህል ከለሮች እንደሚረዝሙ እንመልከት ።**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሀሙስ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን14

## STEM: መወጣጫ



**ቁሳቁሶች: መወጣጫ ለመስራት የሚያስችሉ ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ነገሮች ለምሳሌ ፣ የወረቀት ፎጣ ወይም የሽንት ቤት ወረቀት ጥቅልሎች ፣ የታጠፈ ካርቶን ወይም ወረቀት ፣ ትንሽ ኳስ ወይም የወረቀት ጥቅል ኳስ ፣**

- ከልጅዎ ጋር በስልክ ወይም በታብሌት ላይ የመወጣጫ ሥዕሎችን ይመልከቱ ።
- ይህን ይበሉ, **ኳሳችን ወደ ታች እንዲንከባለል ትንሽ ከፍ ያለ መወጣጫ ልንሠራ ነው ።**
- መወጣጫ ለመስራት አብረው ይሠሩ ። ኳሱ በቀላሉ ወደታች እንዲወርድ የወረቀት ፎጣውን ጥቅል በመክፈት ቀለል ያለ ማድረግ ይችላሉ ። በመቀጠል ጠፍጣፋ ላይ ያስተኙት ወይም ከፍ አድርገው ቁልቁለታማ ያድርጉት እና ኳሱ እንዴት እንደሚንከባላል ያነፃፅሩ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ የኔ መዝናኛ ፓርክ

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ከለሮች ወይም ውሃማ ቀለም ፖሌት**

- ከልጅዎ ጋር በስልክ ወይም በታብሌት ላይ የመዝናኛ ፓርኮች ሥዕሎችን ይመልከቱ ። ስለ መጓጓዣ አይነቶች እና ስላስተዋላቸው ሌሎች ነገሮች ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ልጅዎ ራሱን ችሎ የራሱን የመዝናኛ ፓርክ ዲዛይን እንዲያደርግ ፣ እንዲስል እና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ መዝናኛ ፓርክህ ንገረኝ ። ምን ዓይነት መጓጓዣዎች አሉዎት?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሐሙስ




## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የሶስት–ደረጃ ትዕዛዞችን በመከተል ክለሳ

- ይህን ይበሉ, **ተከተለኝ የተሰኘውን ጨዋታ እንጫወት ። በጥንቃቄ ማዳመጥህን እንዳትዘነጋ!**
- ለልጅዎ ባለ ሶስት - ደረጃ ትዕዛዞችን ይስጧቸው እንደ : ማሽከርከር ፣ መዝለል ፣ ከዚያ ማጨብጨብ ወይም እጆቹን ማሽከርከር ፣ ጉልበቱን መንካት እና ከዚያ ፈገግታ ።
- ልጅዎ ትዕዛዞችን እንዲሰጥ ሚናዎችን ይቀያየሩ።

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የመዝናኛ ፓርኮች

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የመዝናኛ ፓርኮች  ጆርናል ገፅ**

- ከልጅዎ ጋር ሮለርኮስተር ማሽከርከር ምን እንደሚመስል ይነጋገሩ።
- ልጅዎ ሮለርኮስተር ማሽከርከር ምን እንደሚመስል ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለፃፍከው ነገር ንገረኝ ። በሮለርኮስተር መሽከርከር ምን ይመስላል ብለህ ታስባለህ?**


ስም: ____________________

ሮለርኮስተር ማሽከርከር ምን ይመስላል?

**PK4 ህንፃ እና ግንባታ**
© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ስም: ________________

ሮለርኮስተር ማሽከርከር ምን ይመስላል?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# አርብ

PK4 **ክፍል** 3 **ሳምንት** 3  **ቀን**15


## **STEM:** የበዛ, ያነሰ, ወይም እኩል

- አንድ እጅን በሁለት ጣቶች እና አንድ እጅን በአምስት ጣቶች ይያዙ ፡፡
- ይህን ይበሉ, **በጣቶች ብዛት መዳነሰው እጅ አመልክት ፡፡** ልጅዎ ሳይቆጥር እንዲመልስ ያበረታቱት ፣ ነገር ግን ለማጣራት መቁጠር ቢያስፈልጋቸው ችግር የለውም ፡፡
- በእያንዳንዱ እጅ የተለያዩ ወይም ተመሳሳይ መጠኖችን በማሳየት 2-3 ተጨማሪ ጊዜዎችን ይድገሙ ፡፡  የትኛው ያነሰ ወይም ብዙ እንዳለው ወይም ተመሳሳይ መጠን ካላቸው እንዲናገሩ ይጠይቋቸው፡፡

## እራሱን የቻለ ትምህርት: ሕንጻውን መቅረጽ

**ቁሳቁሶች**: **መጫወቻ ሊጥ,** **[የመጫወቻ ሊጥ  አዘገጃጀት]**

- ከልጅዎ ጋር ሊሠራው ስለሚፈልገው የተለያዩ ሕንፃዎች ይነጋገሩ ፡፡
- ይህን ይበሉ, **የመጫወቻ ሊጡን በመጠቀም የሚፈልገውን አይነት ሕንፃ መሥራት ትችላለህ ፡፡**
- ልጅዎ ራሱን ችሎ ህንፃውን እንዲሠራ ያድርጉ፡፡
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ህንፃህ ንገረኝ ፡፡ ሰዎች እዚያ ምን ያደርጋሉ?**



የመጫወቻ ሊጥ አዘገጃጀት

1 ኩባያ ዱቄት
2 የሻይ ማንኪያ ክሬም ታርደር
1/3 ኩባያ ጨው
1 ኩባያ ውሃ
1 የሾርባ ማንኪያ የአትክልት ዘይት
የሚፈልጉትን የምግብ ቀለም

1. ዱቄቱን ፣ ክሬም ታርደሩን፣ እና ጨው በድስት ውስጥ ይጨምሩ፡፡
2. ውሃ እና የአትክልት ዘይት በድስት ውስጥ ይጨምሩ ፡፡ ከመካከለኛ/ ዝቅተኛ ሙቀት በላይ ፣ ድብልቅውን ያማስሉ ፡፡
3. ድብልቅው መወፈር ከመጀመሩ በፊት የምግብ ቀለሙን ይጨምሩ፡፡
4. ከታች ድስቱ ጀምረው ድብልቁን ማማሰሉን ይቀጥሉ፡፡
5. ከመጫወትዎ በፊት ሊጡ እስኪ ቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ ፡፡ አየር በማያስገባ ማስቀመጫ ውስጥ ያስቀምጡት፡፡


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ የአፕል ትሪ ተቋም ፡፡ እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ፡፡.

# አርብ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 3 ቀን15

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ገፁን ማብራራት


**ቁሳቁሶች**: *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር*

- ይህን ይበሉ, **አንድ ገጽ ይምረጡ እና በገጹ ላይ ምን እየተከናወነ እንዳለ ይግለጹ።**
- እንደነዚህ ዓይነቶቹን ጥያቄዎች በመጠየቅ ልጅዎን በመምራት ሊረዱት ይችላሉ ። **ምን አይነት ቅርፅ አየህ፣** ወይም ፣**ምን አስተዋልክ?**

## Read: *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር*

**ቁሳቁሶች**: *(Tying My Shoes) ጫማዎቼን ማሰር*

- ከልጆ ጋር, አንብቡ (*Tying My Shoes*) *ጫማዎቼን ማሰር*
- በኋላ, ይጠይቁ, **Bobby/ የቦቢ ግብ ምን ነበር? ምን ማድረግ ነበር የፈለገው?**




ጫማዎቼን ማሰር ፅሁፍ በጁሊ ፎውለር ምስል በኬነዲ ኋይት


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሳምንት 4


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4 አጠቃላይ እይታ

## የግንባታ ክለሳ



### በሳምንት ልጆ ይህንን ይማራል:

ስለ ድልድዮች እና ቱቦዎች ይማራሉ እንዲሁም በመጀመሪያዎቹ ሳምንታት የተማሩትን እንደ መጠኖችን ማወዳደር ያሉ ነገሮች ይከልሳሉ ።

### ቁልፍ የቃላት ዝርዝር



**ድልድይ**

ሰዎች ወይም ተሽከርካሪዎች እንደ ወንዝ ወይንም መንገድ ያሉ ነገሮችን ለማቋረጥ የሚያግዝ መዋቅር



**ስሜቶች**

ስሜቶች, እንደ ደስታ ወይም ሀዘን


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ግንኙነቶችን ይፍጠሩ

**አስብበት!**

በዚህ ሳምንት የራሶን ድልድይ ይነድፍሉ እንዲሁም ይገነባሉ። ከዚህ በፊት ስላዩት ድልድይ ይጻፉ እንዲሁም ይሳሉ ።  ስለ ድልድዮች ምን ያውቃሉ?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሰኞ



## STEM: እንቁጠር

- ይህን ይበሉ, **ሲሊ/የሞኝ ድምፆችን በመጠቀም እስከ 15 ድረስ እንቆጥረው ። በምን ድምፅ እንድንቆጥር ትፈልጋላህ?**
- 1-2 ጊዜ ተጨማሪ ይቆጥሩ ። ልጅዎ ድምጾቹን እንዲመርጥ ይፍቀዱለት ፣ ለምሳሌ ትራክተር

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ የቤት ውስጥ ቧንቧዎች

**ቁሳቁሶች: ባለውሃ ቀለም ፖሌት ወይም ከለሮች ፣ የቀለም ብሩሽ ፣ ወረቀት ፣ አማራጭ - የወረቀት ፎጣ እና የመጸዳጃ ወረቀት ጥቅልሎች**

- ከልጆ ጋር, የቧንቧዎችን ስዕሎች በስልክ ወይም በታብሌት ላይ ይመልከቱ ።
- ይህን ይበሉ, **ቧንቧዎችን ቀለም መቀባት ይችላሉ ።**
- ልጅዎ እራሱን ችሎ በወረቀቱ ላይ ቧንቧዎችን ዲዛይን እንዲያደርግ እና ቀለም እንዲቀባ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ቧንቧ ለምን እንፈልጋለን? ቧንቧዎች የት ይገኛሉ?**
- ልጅዎ የወረቀቱን ፎጣ እና የመፀዳጃ ወረቀት ጥቅልሎችን ቀለም መቀባት እና ከደረቁ በኋላ ቧንቧ ለመገንባት መጠቀም ይችላል ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሰኞ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4  ቀን16

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ: ባለ ሶስት- ሲላብል ቃላትን ማደባለቅ

- ይህን ይበሉ, **ዛሬ, ባለሦስት ሲላብል ቃላትን እናደባልቃለን ። እነዚያ ሶስት ምት ያላቸው ቃላት ናቸው ። እንደ construction ያሉ ቃላት**
- **ከኔጋ ሶስት ጊዜ አጨብጭብ**: con-struc-tion.
- ይህን ይበሉ, **ሲላብል እንቀላቅል!**
- **ሶስት ሲላብል እነግርሃለው:: አንድ ላይ ሰብስቧቸው እና ቃሉን ንገሩኝ ። Blue** ( ላፍታ ቆም በል) **ber** ( ላፍታ ቆም በል) **ry. Blue-ber-ry. ቃሉ ምንድን ነው?**
- ብዙ ውዳሴ መስጠትዎን አይርሱ! **ጥሩ ስራ!**
- ይድገሙ ለ rectangle/አራት መዖዘን(rec-tan-gle) እና amusement /መናፈሻ (a-muse-ment).
- ልጅዎ ብዙ መለማመድ ቢያስፈልገው ችግር የለውም!

## አንብብ: ***(Mr. Star's New Home)*** የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት

**ቁሳቁሶች**: *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት*

- አንብቡ *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት* በጋራ.
- በኋላ, በገጽ 8 እና 15 መካከል አንድ ገጽ ይምረጡ እና ልጅዎ ያ ማሽን ምን እየሰራ እንደሆነ እንዲገልጽ ይጠይቁ። ይህን ይበሉ, **ይህ ማሽን ምን እያደረገ ነው? ስሙን ታስታውሳለህ?**





© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ማክሰኞ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4  ቀን17

## STEM: የኔን ድልድይ ዲዛይን ማድረግ

**ቁሳቁሶች: እርሳስ ወይም ከለሮች ፣ ወረቀት ፣ ቴፕ ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ነገሮች ለምሳሌ እንደ ትንሽ ፕላስቲክ ኮንቴይነሮች ፣ የወረቀት ፎጣ ጥቅልሎች**



- ከልጅዎ ጋር የድልድዮች ስዕሎችን በስልክ ወይም በታብሌት ላይ ይመልከቱ።
- ይህን ይበሉ, **በሌላ ቀን እነዚህን ነገሮች በመጠቀም ድልድይ ትስራለህ። በመጀመሪያ ድልድይህን መሳል እና ዲዛይን ማድረግ ይኖርብሃል።**
- ልጅዎ የራሱን ድልድይ እራሱን ችሎ እንዲስል እና ዲዛይን እንዲያደርግ ይፍቀዱለት ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ድልድይህ ንገረኝ ። መኪኖች ይነዱበታል ወይንስ ሰዎች ብቻ ናቸው የሚራመዱት?**
- ልጅዎ ቀን 19 ላይ መገንባት እንዲችል ዲዛይን እና ዕቃዎቹን ያስቀምጡ ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ እችላለሁ!

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, ወረቀት**

- ይህንን ይበሉ, **ትንሹ Lief Loader/ሊፍ ሎደር የኮከብን /Star ቤተሰብ መርዳት እንደሚችል ተረዳ ።  እናም Bobby /ቦቢ ጫማዎቹን ማሰር ተማረ ።**
- ይህንን ይበሉ, **ማድረግ ስለሚችላቸው ነገሮች መጻፍ ትችላለህ።**
- ልጅዎ እራሱን ችሎ ሊሰራቸው ስለሚችላቸው ነገሮች እንዲጽፍ እና እንዲስል ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **እባክህን ልትሰራቸው ስለምትችላቸው ነገሮች ንገረኝ ።**



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ማክሰኞ



## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ የገፀ ባህሪ ግብ

**ቁሳቁሶች**: *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት*




- ይህን ይበሉ, **የዚህን መጽሐፍ ጥቂት ገጾች አነባለሁ ። በታሪኩ ውስጥ ስላለው ገፀ ባህሪ ግብ እንድታስቡ እፈልጋለሁ ። ግቡ ገፀ ባህሪው ሊያገኘው ወይም ሊያደርገው የሚፈልገው ነገር ነው ።**
- ኣንብብ ገፅ.4-5 of *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት*።
- ይጠይቁ, **ግቡ ምን ነበር?** ለአፍታ ቆም ይበሉ **ትንሹ Lief Loader/ሊፍ ጫኝ የአቶ ኮከብን /Star አዲስ ቤት ለመገንባት ሊረዳ ነበር ። 's new home.**

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ ቤት መገንባት

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, ቤት መገንባት ጆርናል ገፅ**


ስም: ________________

ቤት መገንባት ቢችሉ ኖሮ ቤትዎት ምን ይመስላል ነበር?

- ቤት ስለመገንባት ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ልጅዎ ሊገነባ ስለሚፈልገው ቤት ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለፃፍከዉ ነገር ንገረኝ ። ቤትህ ምን ይመስላል?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ስም: ________________

ቤት መገንባት ቢችሉ ኖሮ ቤትዎት ምን ይመስላል ነበር?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4  ቀን18

## **STEM:** ቡድኖችን ማወዳደር

- በእያንዳንዱ እጆችዎ ሶስት ጣቶች ይያዙ/ያውጡ።
- አንዱን እጅ ያሳዩ እና ይጠይቅ, **ይህ ከሌላው እጅ የበለጠ ፣ ያነሰ ፣ ወይስ ተመሳሳይ መጠን አለው? አዎ ተመሳሳይ ነው ።**
- **ጨዋታ እንጫወት። ተመሳሳይ መጠን ወይም ሌላ መጠን በጣቶችህ እንድታሳየኝ እጠይቅሃለው ።**
- ተመሳሳይ መጠን በመጠየቅ ሁለት ጊዜ ይጫወቱ ። ከዚያ ወደ አንድ እጅ ይጠቁሙና እንዲህ ይበሉ, **ይህ እጅ ከሌላው ያነሰ እንዲኖረው እናድርግ ፣ የተወሰኑ ጣቶችን ልቀንስ / ልጠፍ ።** ተጨማሪ ይድገሙ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ የመገለል ስሜት

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ኮለሮች ወይም ውሃማ ቀለም ፖሌት እና የቀለም ቡርሽ**

- ከልጆ ጋር, እንደተገለሉ ስለ ተሰማዎት ጊዜ ይናገሩ. ይህን ይበሉ, **አንዳንድ ጊዜ እንደተገለልን ሊሰማን ይችላል ። ትንሹ Lief Loader/ሊፍ ጫኝ ፣ ለመርዳት በሌሎቹ ማሽኖች ባልተፈቀደለት ጊዜ እንደተገለለ ተሰማው ።**
- **እንደተገለልክ ስለ ተሰማህን ጊዜ ሳል።**
- በኋላ, ይህንን ይበሉ, **ስለ ስዕልህ ንገረኝ። እንደተገለልክ በሚሰማህ ጊዜ ጥሩ ስሜት እንዲሰማህ ምን ታደርጋለህ?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ


PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን18

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ባለ ሶስት-ሲላብል ቃላትን ማደባለቅ ክለሳ

- ይህን ይበሉ, **ቃል ለመፍጠር ሶስት ሲላብል እናደባለቅ!**
- **ሶስት ሲላብል እናገራለው ። አንድ ላይ ሰብስባቸው እና ቃሉን ንገረኝ. An** (ላፍታ ዝም ይበሉ) **i** (ላፍታ ዝም ይበሉ) **mal. An-i-mal. ቃሉ ምንድን ነው?**
- ይድገሙ ለ ambulance/አንቡላንስ (am-bu-lance) እና strawberry/ስትሮበሪ (straw-ber-ry). ልጅዎ እንዲነግሩት ከፈለ፣ ችግር የለውም አሁንም እየተማሩ ነው!

## አንብብ፡ ***(Mr. Star's New Home)*** *የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት*

**ቁሳቁሶች**: *[(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት]*




- አንብብ *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት* together.
- በኋላ ,ይጠይቁ, **ትንሹ Lief Loader/ሊፍ ሎደር ሌሎቹ ማሽኖች የእርሱን እርዳታ በማይፈልጉበት ጊዜ ሊትል ሊፍ ሎደር ምን ተሰማው? ጥሩ ስሜት እንዲሰማው ለመርዳት ምን ልትለው ትችላለህ?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ረቡዕ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን18

## እንቅሳቀስ፡ የግንባታ ተግባራትን ማስመሰል

- ይህን ይበሉ, **እንጫወት ። የተለያዩ ተግባራትን የምንከውን እናስመስላለን እና ሳንንቀሳቀስ ባለንበት እንቆማለን።**
- ይህን ይበሉ, **አንድ ነገር ወደ ላይ ከፍ እንደሚያደርግ እንደ ክሬን እንናስመስል ።** ሞዴል ።
- ሌሎች አስታየቶችን /ሀሳቦችን ይስጡ : ጉድጓድ እንደምትሰረስር አስመስል , ሬንች / መፍቻ እየተጠቀምክ እንዳለ አስመስል, ወ.ዘ.ተ.
- ሚና ተቀያየሩ። ልጆ ተግባራትን ማስመሰል ላይ የራሱን ሀሳብ /አስተያየት እንዲሰጥ ያድርጉ።

## በጋራ መማር፡ የቤተሰብ ምሽግ መገንባት

**ቁሳቁሶች: እንደ አንሶላ ፣ ትራሶች ፣ አልጋዎች ፣ ወንበሮች ፣ ሶፋ ያሉ የቤት ዕቃዎች**

- ይህን ይበሉ, **አብረን የምንቀመጥበት የቤተሰብ ምሽግ ወይም ድንኳን እንሥራ ።**
- ከልጅዎ ጋር በታብሌት ወይም በስልክ ላይ የተለያዩ በቤት ውስጥ የተሰሩ ምሽግ ወይም ድንኳኖች ስዕሎችን ይመልከቱ ።
- ምሽጉን በጋራ ያቅዱ እንዲሁም ይገንቡ ። 2 ተራርቀው የተቀመጡ ወንበሮችን በአንሶላ በመሸፈን / በማልበስ ቀለል ያለ ምሽግ ማድረግ ትችላላችሁ ። ወይም ፣ ሌሎች ዕቃዎች በመጠቀም ትልቅ ምሽግ ማድረግ ትችላላችሁ ።


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሀሙስ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4  ቀን19

## STEM: የኔን ድልድይ መገንባት

**ቁሳቁሶች: በ 17ኛው ቀን ላይ የተሰራው የድልድይ ዲዛይን ፤ ቴፕ ፤ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ በሚችሉ ነገሮች ላይ እንደ ትናንሽ ፕላስቲክ ኮንቴይነሮች ፤ የወረቀት ፎጣ ጥቅልሎች**

- ለልጅዎ የድልድይ ዲዛይኑን ያሳዩ እና ድልድዩን ስለመገንባት ያነጋግሩ ::
- ይጠይቁ, ድልድይዎን ለመሥራት ምን ዓይነት ቁሳቁሶችን ትጠቀማለህ?  መጀመሪያ ምን ታደርጋለህ?
- ልጅዎ ድልድዩን እራሱን ችሎ እንዲገነባ ይፍቀዱለት ::
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለ ድልድይህ ንገረኝ፡፡**

## እራሱን የቻለ ትምህርት : በድልድዬ ላይ ያሳለፍኩት ቀን

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, ወረቀት**

- ይህን ይበሉ, **አሁን ድልድይ ሰራህ ። አሁን ፣በድልድይዎ ላይ ስላሳለፍከው ቀን ታሪክ ፅሁፍ ፃፍ ወይም ስዕል ሳል፡፡  በድልድይዎ ላይ ምን ተከናውነ?**
- ልጅዎ በድልድዩ ላይ ባሳለፈው ቀን የተፈጠረውን ነገር ራሱን ችሎ እንዲጽፍ ወይም እንዲስል ይፍቀዱለት፡፡
- በኋላ, ይጠይቁ, **እባክህን በድልድይህ ላይ ባሳለፍከው ቀን ላይ ስለነበረው ነገር ልትተርክልኝ ትችላለህ?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# ሀሙስ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4  ቀን19

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ እናደባልቅ!

- ይህን ይበሉ, **ቃል ለመመሰረት ሁለት እና ሶስት ሲላብል እናጣምር!**
- **ሁለት ወይም ሦስት ሲላብል እናገራለሁ ። አንድ ላይ ሰብሰባቸው እና ቃሉን ተናገር ። Door /ዶር** ( ላፍታ ዝም በል) **way/ ዌይ. Door-way. /ዶር- ዌይ ቃሉ ምንድን ነው ?**
- ይድገሙ ለ window /ዊንዶ (win-dow) and frustrated /ፍረስትሬትድ (frus-trat-ed). ልጅዎ እንዲነግሩት ከፈለ፣ ችግር የለውም አሁንም እየተማሩ ነው!

## የፅሁፍ ሃሳብ፡ የምኖርበትን ለምንድን ነው የምወደው

**ቁሳቁሶች: ከለሮች, የምኖርበትን ለምንድን ነው የምወደው ጆርናል ገፅ**

- ስለሚኖሩበት ከተማ ወይም መንደር ከልጅዎ ጋር ይነጋገሩ።
- ልጅዎ ስለ ከተማው ወይም ስለ መንደሩ በጣም የሚወደው ነገር እራሱን ችሎ እንዲሳል እና እንዲጽፍ ያድርጉ ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለፃፍከው ነገር ንገረኝ። በምትኖርበት ቦታ ምንድን ነው በጣም የምትወደው?**





© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

ስም: ________________

በሚኖሩበት ቦታ ምንድን ነው በጣም የሚወዱት?


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# አርብ

PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4 ቀን20

## STEM: የበለጠ ወይም ያነሰ ያድርጉት

- በእያንዳንዱ እጅዎ አንድ ጣት ወደ ላይ ይያዙ ። ይጠይቁ, **ጣቶቼ ተመሳሳይ ቁጥር ይዘዋል ወይስ አንዱ ተጨማሪ አለው? አዎ ተመሳሳይ ናቸው ።**
- ይጠይቁ, **ይህ** (የግራ እጅ) **ከዚህ** (የቀኝ እጅ) **የበለጠ እንዲኖረው ምን አደርጋለሁ? አዎ ፣ ተጨማሪ ጣቶችን ማንሳት እችላለሁ ።** ሞዴል.
- **አሁን አንተ ትሞክራላህ ። በሁለቱም እጆች ላይ ተመሳሳይ ጣቶችን አሳየኝ ። አሁን ፣ ይህኛው ትንሽ ጣቶች እንዲኖሩት አድርግ ፣ የተወሰኑትን እጠፍ።**
- 1-2 ያህል ተጨማሪ ጊዜ ይድገሙት, አንድ እጅ የበለጠ ወይም ያነሱ ጣቶች እንዲኖሩት ልጅዎን ይጠይቁት። ልጅዎን እንደአስፈላጊነቱ ይርዱት ።

## እራሱን የቻለ ትምህርት ፡ የህንፃ ግንባታን ይሰናበቱ

**ቁሳቁሶች: ወረቀት, ከለሮች**

- ይህን ይበሉ, **ስለ ግንባታ ስንማር ቆይተናል።** ከልጅዎ ጋር ስለ ህንፃ ግንባታ ከተማረው መሃል ስለወደው ክፍል ተነጋገሩ። የእርሱ ተወዳጅ እንቅስቃሴ ወይም መጽሐፍ ሊሆን ይችላል።
- ልጅዎ በዚህ ክፍል/ ዩኒት ዉስጥ ልጆ ስለሚወደው ክፍል ራሱን ችሎ እንዲስል እና እንዲጽፍ ያድርጉ።
- በኋላ, ይጠይቁ, **ስለምንድን ነው የፃፍከው? ያንተ ተወዳጅ የሆነው ለምንድን ነው?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

# አርብ


PK4 ክፍል 3 ሳምንት 4  ቀን20

## ፅሁፍ መፃፍ እና ማንበብ፡ ባለ ሁለት እና ሶስት ደረጃ ትዕዛዝ በመከተል

- ይህን ይበሉ, **ተከተለኝን እንጫወት። የምናገረውን አዳምጥ። ከዚያ አድርግ!**
- ለልጅዎ ሁለት-ደረጃ እና ሶስት-ደረጃ ትዕዛዞችን ይስጡት፡ ጆሮህን ንካ ፣ ከዚያ አገጭህን ንካ ፣ ራስህን ንካ ፣ ይሳቅ ፣ ከዚያ ጣቶቹን ማስጮህ /ስናኘ ዩር ፈንገር ፣ ወዘተ ።
- ልጅዎ ትዕዛዞችን እንዲሰጥ ሚናዎችን ተቀያየሩ።

## አንብብ፡ ***(Mr. Star's New Home)*** *የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት*


**ቁሳቁሶች**: *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት*




- አንብብ *(Mr. Star's New Home) የአቶ. ኮከብ አዲስ ቤት ።*
- በኋላ, ይጠይቁ, **ቤት በምንሠራበት ወቅት ለምንድን ነው ብዙ የተለያዩ ማሽኖች የሚያስፈልጉን?**


© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.

**ወደ ክፍል 3 እንኳን በደህና መጡ! በክፍል 3 ውስጥ ልጅዎ ስለ የግንባታ ሂደት ይማራል - ንድፍ ማውጣት ፣ የግንባታ ሰራተኞችን እና የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች ያካትታል።**



© 2020 መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው። የአፕል ትሪ ተቋም ። እያንዳንዱ ልጅ ዝግጁ።.